# የገንዘብ ሚኒስቴር

## ባልተከፋፈለ ትርፍ ላይ ስለተጣለው ግብር አፈፃፀም

## የወጣ መመሪያ ቁጥር 7/2011

የገንዘብ
የሪከርድ
አስተዳደር
አገልግሎት
2
ሚኒስቴር

ገንዘብ ሚኒስቴር

2011 ዓ.ም

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

የታክስ ከፋይ ምዝገባ/GT

# ባልተከፋፈለ ትርፍ ላይ ስለተጣለው ግብር አፈፃፀም
## <u>የወጣ መመሪያ ቁጥር 7/2011</u>

1. <u>አውጪ ባለሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስትሩ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 61 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### <u>ጠቅላላ</u>

2. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ 'ባልተከፋፈለ ትርፍ ላይ ስለተጣለው ግብር አፈፃፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 7/2011' ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. <u>ትርጓሜ</u>

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 እና በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ትርጉም የተሰጠው ቃል በእነዚህ አዋጆች የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም፡-

1. "ያልተከፋፈለ ትርፍ" ማለት የድርጅቱ የሂሳብ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ባለው የ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ለባለአክሲዮኖች ያልተከፋፈለ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ባቋቋመው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት አማካኝነት የንግድ ሥራ ለሚያካሄድ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ ድርጅት ያልተላከ ትርፍ ወይም የኩባንያውን ካፒታል ለማሳደግ ያልዋለ የተጣራ ትርፍ ነው፡፡
2. "የተጣራ ትርፍ" ማለት በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት በተሰላው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ ኩባንያው ሊከፍል የሚገባው የንግድ ትርፍ ከተከፈለ በኋላ ሌሎች የማህበሩ ወጪዎች እንዲሁም አላቂ ለሆኑት ነገሮች መተኪያ ገንዘብና የገንዘብ ስንቆች ሁሉ በሂሳብ ጊዜው ከተገኘው ጠቅላላ ገቢ ላይ ተቀንሰው የሚገኘው ትርፍ ነው፡፡
3. "ባለስልጣን" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም የአዲስ አበባ ወይም የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የገቢዎች ባለስልጣን ነው፡፡
4. "አዋጅ" ማለት የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ነው፡፡

4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ያገኙትን ትርፍ በሙሉ ወይም በከፊል እንዳያከፋፍሉ በህግ ከተከለከሉት በስተቀር ያልተከፋፈለ ትርፍ ባላቸው ማናቸውም ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## <u>ባልተከፋፈለ ትርፍ ላይ ግብር የሚከፈልበት ስርዓት</u>

5. <u>ግብር ስለመክፈል</u>

1. ያልተከፋፈለ ትርፍ በአዋጁ አንቀጽ 61 መሰረት አስር በመቶ (10%)ግብር ይከፈልበታል፡፡

2. አንድ ድርጅት ባልተከፋፈለ ትርፍ ላይ ግብር እንዲከፍል የማይጠየቀው ድርጅቱ በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ የተገኘውን ያልተከፋፈለ ትርፍ የሂሳብ ጊዜው በተጠናቀቀ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ የአባላቱን የአክስዮን ድርሻ መጠን እና የድርጅቱን ካፒታል በተገኘው የተጣራ ትርፍ መጠን ካሳደገ ነው፡፡ ሆኖም የተጣራው ትርፍ ያልተከፋፈለው የትርፍ ድርሻ ከፊል ከሆነ የዚህ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው ባልተከፋፈለው የትርፍ መጠን ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

3. ያልተከፋፈለ ትርፍ ያለው ድርጅት በዚህ መመሪያ መሠረት የተጠቀሰው የ12 ወራት ጊዜ ካበቃ በኋላ ባለው 2 (ሁለት) ወር ጊዜ ውስጥ ግብሩን አስታውቆ መክፈል ይኖርበታል፡፡

6. <u>ማስረጃዎችን ስለማቅረብ</u>

1. አንድ ድርጅት ያልተከፋፈለ ትርፍ የሌለው መሆኑን ለመወሰን እንዲቻል ቀጥሎ የተመለከቱትን ማስረጃዎች ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

   ሀ) በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ የተገኘው የተጣራ ትርፍ ለባለአክስዮኖች የተከፋፈለ ወይም የባለአክስዮኖችን የአክስዮን ድርሻ መጠን ለማሳደግ የዋለ መሆኑን የሚያረጋግጡ እንደቅደም ተከተላቸው በተከፋፈለው የትርፍ ድርሻ መጠን ልክ ግብር ስለመክፈሉ ወይም የድርጅቱ ካፒታል ስለማደጉ የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣

ለ) የአባላት የአክስዮን ድርሻ እና የድርጅቱ ካፒታል ስለማደጉ የሚቀርቡ ማስረጃዎች እንደአግባብነቱ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ወይም አግባብነት ባለው የክልል/የከተማ አስተዳደር ቢሮ የጸደቀ የድርጅቱ ቃለጉባዔ እና ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም አግባብነት ባለው አካል/ንግድ ቢሮ የድርጅቱ ካፒታል ስለማደጉ የሚገልጽ ሰነድ፣

2. ድርጅቱ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ያገኘውን የተጣራ ትርፍ ለባለአክስዮኖች ሳያከፋፍል የአክስዮን ድርሻቸውን መጠን ለማሳደግ ያዋለው ከሆነ ይኸንኑ የሂሳብ ጊዜው ካበቃ በኋላ ያለው የ12 ወራት ከተጠናቀቀ በኋላ ባለው 2 (ሁለት) ወር ወይም ቀደም ብሎ ባለው ጊዜ ውስጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሱ ማስረጃዎችን በማያያዝ ለባለስልጣኑ ማስታወቅ አለበት፡፡

## 7. <u>ባልተከፋፈለ ትርፍ ላይ ግብር ያለመክፈል ውጤት</u>

1. አንድ ድርጅት ያልተከፋፈለ ትርፍ ኖሮት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5(3) በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ግብሩን ያላስታወቀ እና ያልከፈለ እንደሆነ ከሚከፈለው ፍሬ ግብር በተጨማሪ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 104 እና 105 መሰረት አስተዳደራዊ መቀጫ ይጣልበታል፤ እንዲሁም ባልተከፈለው ፍሬ ግብር ላይ ወለድ ይከፍልበታል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተው ቢኖርም ድርጅቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5(2) በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ትርፉን የባለአክስዮኖችን ድርሻ ለማሳደግ ያዋለው ሆኖ ይህንኑ በመመሪያው አንቀጽ 6(2) በተጠቀሰው መሰረት ያላስታወቀ እንደሆነ ፡-

ሀ) በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የባለአክስዮኖችን ድርሻ ስለማሳደጉ በድርጅቱ ላይ ግብር ከመወሰኑ በፊት ከታወቀ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 104(5) መሰረት አስተዳደራዊ መቀጫ ብቻ ይጣልበታል፡፡

ለ) በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የባለአክስዮኖችን ድርሻ ስለማሳደጉ በድርጅቱ ላይ ግብር፣ አስተዳደራዊ መቀጫ እና ወለድ ከተወሰነ በኋላ የታወቀ ከሆነ ደግሞ የተወሰነበት ግብር ክፍያ በዘገየበት የሚከፈል መቀጫ እና ወለድ ቀሪ ሆኖ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 104(1) መሠረት ባለማስታወቅ የሚጣለውን አስተዳደራዊ መቀጫ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

3. አንድ ድርጅት የድርጅቱን ትርፍ የባለአክስዮኖቹን ድርሻ ለማሳደግ ያዋለው የሂሳብ ጊዜው በተጠናቀቀ ከ12 ወራት በኋላ ከሆነ መብቱን እንደተወው እና ያልተከፋፈለ ትርፍ እንዳለው ስለሚቆጠር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 በተመለከተው መሰረት ግብሩን፣ አስተዳደራዊ መቀጫ እና ወለድ ይከፍላል፡፡

## 8. የትርፍ ድርሻ ግብርን ቀሪ ስለማድረግ

ባልተከፋፈለ ትርፍ ላይ ግብር ከተከፈለ በኋላ ድርጅቱ ትርፉን ለባለአክስዮቾች ያከፋፈለ እንደሆነ በአንድ ገቢ ላይ ሁለት ጊዜ ግብር መጠየቅ ስለማይቻል በአዋጁ አንቀጽ 55 መሰረት የሚከፈለው የትርፍ ድርሻ ግብር ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## 9. በግብር እፎይታ ላይ ያለ ድርጅት

በግብር እፎይታ ላይ ያለ ድርጅት ያገኘውን የተጣራ ትርፍ ለባለአክሲዮኖች ካከፋፈለ በአዋጁ አንቀጽ 55 ወይም የተጣራ ትርፉን ለካፒታል ማሳደጊያነት ካላዋለው ወይም ለባለአክሲዮኖች ካላከፋፈለው በአዋጁ አንቀጽ 61 መሠረት ሊከፈል የሚገባውን ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

## 10. ስለህብረት ስራ ማህበራት የግብር አከፋፋል ሁኔታ

1. ስለህብረት ስራ ማህበራት በወጣው አዋጅ ቁጥር 985/2009 መሰረት ማንኛውም የህብረት ስራ ማህበር ካገኘው ትርፍ ላይ 30 በመቶውን ለካፒታል ማሳደጊያ ካዋለው በኃላ የቀረውን ትርፍ ግለሰብ ላልሆኑ አባላት የሚያከፋፍል ሲሆን ግለሰብ ላልሆኑ አባላት የሚያከፋፍለው ትርፍ ከትርፍ ድርሻ ግብር ነፃ ነው፡፡ ሆኖም ግለሰብ ለሆኑ አባላት የሚከፋፈለው የትርፍ ድርሻ ግብር ይከፈልበታል፡፡

2. የሕብረት ስራ ማህበር አባላት ያገኙትን ትርፍ ለካፒታል ማሳደጊያ የሚያውሉት ከሆነ ይህን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከህብረት ስራ ኤጀንሲ ወይም አግባብነት ካለው አካል በማቅረብ ካልተከፋፋለ ትርፍ ግብር ነጻ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

3. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 የተደነገገው ቢኖርም የኅብረት ሥራ ማህበራት ግለሰብ ለሆኑ አባላት ባልተከፋፈለ የትርፍ ድርሻ ላይ ግብር እንዲከፍሉ የሚጠየቁት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን መረጃ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሳብ ኦዲት ከተደረገ በኋላ ባለው ያ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ለታክስ ባለሥልጣኑ ካላቀረቡ ነው፡፡

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

11. **የተሻሩ መመሪያዎች**

በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብበር ሚኒስቴር ሐምሌ 30/2005 በቁጥር ገ/ኢ/1/2/3 የወጣው መመሪያ በባለስልጣኑ ይህን መመሪያ ለማስፈጸም የተላለፉ ደብዳቤዎች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

12. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከ2009 የሂሳብ ዓመት ጀምሮ በተገኘና ባልተከፋፈለ የትርፍ ድርሻ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም ከኢትዮጵያ የበጀት ዓመት የተለየ የሂሳብ ጊዜን ለሚጠቀሙ የአዋጁ አንቀጽ 28(6) ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ ግንቦት 16 ቀን 2011 ዓ.ም.*

*አህመድ ሺዴ*
*የገንዘብ ሚኒስትር*